የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order
www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ያሬድ

*በእደ ማርያም እጅጉ ረታ*

ታላቁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዜማ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ በ493 ዓ.ም በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት በአክሱም ተወለደ። ዕድሜውም ለትምህርት እንደደረሰ በአቅራቢያዉ ወደሚገኘው ቤተ ክርስቲያን እየተመላለሰ ከመምህር ይስሐቅ እንዲሁም ከአጎቱ አባ ጌዴዎን ዘንድ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያንትምህርቱን መማር ጀመረ። ያሬድ ከመወለዱ 3 ዓመታት (490 ዓ.ም) በፊት ተስዐቱ ቅዱሳት ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት፣ ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚካሄድበትና ገዳማት የተመሠረቱበት ወቅት ነበር። ያሬድም ከአጎቱ አባ ጌዴዎን ዘንድ ሲማር በተጨማሪም ከእነዚህ አባቶች አንዱ ከሆኑት ከአባ አረጋዊ ዘንድ ተምሯል።

ቅዱስ ያሬድ የመማር ችግር እንደነበረበትና ትምህርቱ አልገባው እያለ ተስፋ ቆርጦ ዳግም ወደ መምህሩ ላይ መለስ ወስኖ እንደነበር ነገር ግን አንድ ቀን ዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጦ አንድ ትል ወደ ዛፉ አናት ለመውጣት ሲታገል፣ መሐል ላይ ሲድርስና ተመልሶ ሲወድቅ፣ እንደገና ያለመታከት ሲሞክርና በመጨረሻም ዛፉ አናት ላይ ወጥቶ ቅጠልዋን ሲበላ ተመለከተ። ከዚህ ትል በመማር ተመልሶ ወደ መምህሩ በመሄድ ትምህርቱን ቀጠለ። ትምህርቱን እየተከታተለ ሳለ የዕውቀት ምስጢር እንደተገለጸለትና እስካሁን ድረስ የምንጠቀምበትን አምስቱ ፀዋትዎ ዜማዎችን በተለያዩ ጊዜያት በመድረስ አስተላልፎልናል። የዜማዎቹ ይዘት ሲታይ ቅዱስ ያሬድ ጥልቅ የሆነ የብሉይ፣ የሐዲስ ኪዳን እንዲሁም የልዩ ልዩ መጻሕፍት ዕውቀት እንደነበረዉ ለመረዳት አያዳግትም። እርሱ እዚህን ጣዕመ ዜማዎች እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ በቤተ ክርስቲያን የጸሎት አገልግሎት ይካሄድ የነበረው ከፍ ባለና በለሆሳስ ድምፅ ነበር። ስለዚህ ቅዱስ ያሬድ ዜማን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያስጀመረ ነው።

ከታሪኩ እንደምንረዳው ቅዱስ ያሬድ አንደበተ ቀና (ድምጸ መረዋ) ስለነበር በሚዘምርበትም ጊዜ በወቅቱ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ገብረ መስቀል፣ ካህናት እና ምእመናን ተሰብስበዉ ቀኑን ሙሉ ሲያደምጡት ይውሉ ነበር። ቅዱስ ያሬድ በአንድ ወቅት በታላቅ ተመስጦ ሲዘምር ዐፄ ገብረ መስቀል ሳያውቁ በጦራቸዉ የእግሩን ጣት ወጉት ይሁን እንጂ ቅዱስ ያሬድ አልተሰማውም ነበር። ዐፄ ገብረ መስቀል ሳያውቁት ላደረሱበት አደጋ የጠየቀውን ሊሰጡት ቃል ገቡለት። ቅዱስ ያሬድም ዜማውን በተመስጦ ለመድረስ እንዲችል ከዚያ አካባቢ ርቆ ወጣ ወዳለ አካባቢ እንዲሄድ እንዲፈቀድለት ጠየቀ። ምንም እንኳ ዐፄ ገብረ መስቀል በጥያቄው ደስተኛ ባይሆኑም ቃል ስለገቡለት እንዲሄድ ፈቀዱለት። ቅዱስ ያሬድ እስከ ዐረፈበት ግንቦት11 ቀን ድረስ በብት ሕውና ኖረ። አንዳንዶች በጣና ቂርቆስ ኖሮ ነው የሞተው ይላሉ። በዚህም ታላቅ ገዳም ያሬድ የጻፈው የድጓ መጽሐፍ ይገኛል።

የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት የተደረሱት ምስጢራቸው ለየወራቱ፣ ለበዓላትና ሰንበታት፣ ለመላእክት፣ ለቅዱሳን፣ ለነቢያት፣ ለሰማዕታት መድቦ አዘጋጀቸው። ዜማዎቹ ሦስት ዓይነት ማለትም ግእዝ፣ አራራይና ዕዝል ሲሆኑ እንደ ወራቱናወቅቱ ጸሎቱ ይደርሳል። የድርሰቱ ይዘት፣ ብዛት፣ ጥልቅ መልእክቱ ሲታይ ከላይ እንደ ተገለጸው የዕውቀት ምስጢር በመንፈስ ቅዱስ ካልተገለጸለት በስተቀር በተራ ሰው ሕሊና ታስቦ የተጻፈ ነው ሊባል አይቻልም።

የቅዱስ ያሬድ ዜማ በአብዛኛው መቋሚያና ጸናጽል በመያዝ በከበሮ በተቀናጀ ሁኔታ ይዜማል። እነዚህ የዜማ መገልገያ ዕቃዎች ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት በግብጽ ይጠቀሙባቸው እንደ ነበር ታሪካዊ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ። ይሁን እንጂ አሁን የምንጠቀምበት ግብጻውያን ከሚጠቀሙበት በቅርጹ ትንሽ ለየት ይላል። በዐቢይ ጾም ግን ከበሮ አይመታም። ማኅሌት እንዲቆም ሆኖ የተሠራው ሥርዓት ቊጥራቸው 24 በሆኑ ደባትሮችሲሆን ይህም የ24ቱ ካህናተ ሰማይ ምሳሌ ነው። እነዚህም ከሁለት ተከፍለው በግራ ያሉት በግራ ጌታ እየተመሩ ፤ በቀኝ በኩል ያሉት ደግሞ በቀኝ ጌታ እየተመሩ ሁሉም ደግሞ በዋናው መሪጌታ ይመራሉ። ዜማውም በአራት ዓይነት ይባላል፤ መጀመሪያ በቁም ዜማ በድምፅ ብቻ ይባላል። ከዚያ ይዘመማል።

**የሚቀጥለው ክፍል መረግድ ይባላል፤ ይህም በሦስት ይከፈላል« መረግድ(ቀስ ተብሎ የሚዜም)፣ ንዑስ መረግ ድ (ፈጠን ተብሎ የሚዜም)፣ ዓቢይ መረግድ (በጣም ፈጠን ተብሎ የሚዜም)» ሲሆን የመጨረሻው ክፍል ፅፋትና ቸብቸቦ ይባላል። ፅፋት በሁለት ይከፈላል፤ ዓቢይ ፅፋት (እንደ ዓቢይ መረግድ የፈጠነ) እና ፅፋት ( በጣም የፈጠነ)። ተያይዞም በቸብቸቦ በጭብጨባ በፍጥነት ይዜማል።**

**ቅዱስ ያሬድ ከዜማው ድርሰት ባሻገር ሙዚቃን በምልክት የሠራ የመጀመሪያው አፍሪቃዊ ነው። አንዳንዶች ግን ድርሰቶቹ የሙዚቃ ምልክት የተደረገባቸው ከሱ በኋላ በተነሱ ሊቃውንት በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግ ሥት** (1501 - 1532**ዓ.ም**) **ነው ይላሉ።**

**ሌላው የ**6**ኛው ክፍለ ዘመን ቅዱስ ያሬድን ልዩ የሚያደርገው የዜማው አጻጻፍና አቀራረቡ ከ**16**ኛ ክፍለ ዘመን በኋላ ከተነሱት ታላላቅ የክላሲካል ሙዚቃ ጸሐፊዎች (ሐንድል፣ ቤቶቨን፣ ሃይድን፣ ሞዛርት ወዘተ) ጋራ ተመሳሳይነቱ ነው።**

## <u>ጥቂቶቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዜማ ምልክቶች</u>

1. **ይዘት** *yizet* Detached and Accented tone. Derived from the verb *meyaz*, to hold. Equivalent to *staccato.*
2. **ደረት** *deret* Sing in a low , deep voice. Chest register. Also applies to singing with the lips closed, with clenched teeth, and with deep chest resonance. Humming at the lowest range of the male voice.
3. **ቅናት** *kinat* Upward *glissando*. The term is derived from the verb *makenat*, “to raise up.”
4. **ጭረት** *Chiret* Start high and proceed with downward *glissando*. The chirt vocal melody is often connected to a cadence. The term is derived from *chira,* “tail.”
5. **ድፋት** *difat* Drop the voice. Skip to a lower range. Often refers to singing an octave lower. The root verb is medfat, “to throw down.”
6. **ቁርጥ** *Kurt* Refers to singing a cadential formula which often ends on the home tone. Its root is *mekuret,* “to end” or to “to cut.” Equivalent to *coda*.
7. **ሩጥ** *rute* Throbbing, warm and expressive singing style with rapid but narrow pitch fluctuations. The term derived from *merot*, “to run.” Equivalent to *vibrato*.
8. **ርክርክ** *rikrik* Rapid repeat of a single syllablic tone. This style of singing usually creates a sense of tension at the high range. Equivalent to *tremolo*.
9. **ሂደት** *hidet* Gradually getting faster and louder. Sing each syllable distinctly. Equivalent to *accelerando, crescendo,* and *portamento* at the same time.
10. / **ሠረዝ** serez Slight pause.

**የአዘማመሩና ፍጥነቱ እንደ ክላሲካል ሙዚቃው ተመሳሳይነት አለው።**

| **Terms used to indicate rates of speed** | | |
|---|---|---|
| **መረግድ** | *mereged* | Very slow, broad and solemn. Equivalent to *largo* and *grave*. |
| **ንዑሥ መረግድ** | *nuis-mereged* | Slow. Literally "faster than meregd." Equivalent to *adagio*. |
| **አቢይ ፅፋት** | *abiy-tsefat* | Moderately fast. Equivalent to *allegretto.* |
| **ፅፋት** | *tsefat* | Fast. Equivalent to *allegro.* |
| **አርዋጺ** | *arwasti* | As fast as possible. Equivalent to *prestissimo.* |

**ለማጠቃለል ያህል ይህ ታላቅ የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ ሥራው ወይም ታሪኩ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን መላው ኢትዮጵያን ሊኮሩበት፣ ሊማሩት፣ ሊያጠኑት እንዲሁም ለሌሎች ሊያስተዋውቁ ይገባል።**

**ቅዱስ ያሬድ ከዜማ ባሻገር ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥነ ጽሑፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋ ጽኦ ያደረገ፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችንን የትምህርት አሰጣጥ መሠረት የጣለ ነው።**

**ዋቢ መጻሕፍት**


**ከመሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገ/ኢየሱስ፣ጥንታዊ ሥርዓት ማህሌት ዘአቡነ ያሬድ ሊቅ፤ አዲስ አበባ፣** 1997።

Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270, Sergew Hable selassie (Associate Professor) 1972.

Professor Ashenafi Kebede, Roots of Black Music,Prentice-Hall , New Jersey, 1982.


January 2004